Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No. 32
ADDIS ABABA 23[rd] April, 2011

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፮/፪ሺ፫

ለመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ድጋፍ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ጋር የተፈረመው የፋይናንስ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……ገጽ ፭ሺ፰፻፩

CONTENTS

Proclamation No. 706/2011

International Development Association Additional Financing Agreement to Protection of Basic Services Program-Phase II Project Ratification Proclamation Page 5801

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፮/፪ሺ፫

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የፋይናንስ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ድጋፍ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፲፫ሚሊዮን፯፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. /አንድ መቶ አሥራ ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር./ በብድር እንዲሁም ፩፻፷፩ሚሊዮን፯፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. /አንድ መቶ ስልሳ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ. ዲ. አር./ በዕርዳታ የሚያስገኘው የፋይናንስ ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሔደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 706/2011.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 113,700,000 SDR (one hundred thirteen million seven hundred thousand Special Drawing Rights) and a grant amount of 161,700,000 (One hundred sixty one million seven hundred thousand Special Drawing Rights) for Additional Financing to Protection of Basic Services Program –Phase II Project was signed in Addis Ababa on the 10[th] day of March 2011;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 7[th] day of April, 2011;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Ministry of justice



## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ድጋፍ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ጋር የተፈረመው የፋይናንስ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፮/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 4867-ET እና የዕርዳታ ስምምነት ቁጥር H643-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፋይናንስ ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፲፫ሚሊዮን፯፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. /አንድ መቶ አስራ ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር./ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Additional Financing Agreement to Protection of Basic Services Program –Phase II Project Ratification Proclamation No. 706/2011".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 4867-ET and Grant Number H643-ET signed in Addis Ababa on the 10th day of March 2011 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 113,700,000 SDR (one hundred thirteen million seven hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the financing agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 23rd day of April, 2011**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**